
ትውውቅ
አመጽሐፍ ቅዱስ ጋር

ትውውቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር

በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የሚገኘውን ብልጽግና ለማግኘት እገዛ

“የእግዚአብሄርን ቃል ያገኘነው ሕይወታችንን እንዲቀይር ነው እንጂ እውቀታችንን ለመጨመር አይደለም።”

ከጌታ ጋር በየቀኑ

እግዚአብሄር ቃልህን ወይም ሥራህን ብቻ እንደማይፈልግ እወቅ። እንደ አፍቃሪ አባት ከአንተ ጋር ህብረት ማድረግን ይፈልጋል። እርሱን እንድታውቀው በናፍቆት እየጠበቀ ነው እኛም ደግሞ በየዕለቱ ከእርሱ ጋር ጥቂት የተወሰነ ጊዜ እንድታሳልፍ እንመክርሃለን። ይህ ከእግዚአብሄር ጋር ጊዜን እንዴት እንደምታሳልፍ የተሰጠ አስተያየት ነው፡

1. በአጭር ጸሎት ጀምር
2. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሆነ ከፍል አንብብ፣ ምናልባት አንድ ምዕራፍ ጥሩ ርዝማኔ ሊሆን ይችላል። ረጋ ብለህ፣ ለጥቂት ጊዜ አንብበው። ከዚህ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን አንብበህ የማታውቅ ከሆነ፣ በሉቃስ ወንጌል መጀመር መልካም ሊሆን ይችላል። (ሉቃስን አንብብ፣ ከዚያም የሐዋርያት ሥራን፣ ፣ ቆሮንቶስን፣ ዘፍጥረትን፣ ዘጸአትን . . .)
3. ስለ ክፍሉ እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቅ፡
   ሀ) በክፍሉ ውስጥ ዋናው መልእክት ምንድን ነው? ያነበብከውን ክፍል በአንድ ወይም በሁለት አረፍተ ነገሮች አጠቃልል
   ለ) ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሄር ምን አስተማረህ?
   ሐ) በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ሊናገርህ እንደፈለገ የምታምነው የሆነ ግልጽ ነገር አለን?
   መ) በሚቀጥሉት ቀናት ይህ በህይወትህ ላይ ምን ተጽዕኖ ያመጣል? ለእግዚአብሄር ታዛዥ ለመሆን የሆነ ነገር ለማድረግ ትፈልጋለህን?
   ሠ) ይህንን ክፍል አብረኸው ልትካፈለው የምትችል ሰው አለን?

4. ጊዜህን በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ጨርስ።

ሀ) እግዚአብሄርን አመስግን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተማርከው ነገር አመስግነው።

ለ) ይቅር እንዲልህ ጠይቀው። ይቅርታ የምትጠይቅበት ግልጽ የሆነ ነገር አለህን? ይቅር ሊልህ እንሚፈልግ እወቅ!

ሐ) ስሚያስፈልጉህ ነገሮች ጸልይ

መ) ለሌሎች ጸልይ

የእግዚአብሄር ቃል

ምክሩ የእግዚአብሄርን ቃል በየዕለቱ እንድታነብ ነው፣ እግዚአብሄር በቃሉ በኩል ልብህን ይነካል! በራሱ ህይወትና እውነት ይሞላሃል! የእግዚአብሄር ቃል፡
ህያውና የሚሰራ ነው፡ ዕብራውያን 4፡12-13
የእግዚአብሄር እስትንፋስ ነው፣ ለማስተማርና ለበጎ ሥራ ለማዘጋጀት የሚጠቅም ነው፡ 2 ጢሞቴዎስ 3፡14
ለልብ ደስታን የሚሰጥ ነው፡ መዝሙር 19፡8-12፣ መዝሙር119
አንተን ነጻ የሚያወጣ ነው፡ ዮሐንስ 8፡31-
እውነት ነው፡ ዮሐንስ 17፡17-19
በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠ ነው፡ 1 ቆሮንቶስ 2፡9-14
በኢየሱስ የተመሰከረ ነው፡ ዮሐንስ 5፡39-47
በአይን ምስክሮች የተጻፈ ነው፡ ሉቃስ 1፡1-4፣ 1 ዮሐንስ 1፡1-4
የፈጠራ ታሪክ አይደለም፡ 2 ጴጥሮስ 1፣16-21
ቃሉ የሚለውን አድርግ፡ ያዕቆብ 1፡22-25

የብሉይ ኪዳን አጭር መግለጫ

ብሉይ ኪዳን መሲሁ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ስላለው ጊዜ የሚያስተምረን 39 ልዩ ልዩ መጽሐፍትን የያዘ ነው። ነብያቱንና ሌሎች የእግዚአብሄር ሰዎችን፡ አዳምን፣ አብርሃምን፣ እስማኤልን፣ ይስሃቅን፣ ያዕቆብንና ሙሴን ዳዊትንና ሌሎችንም እናገኛለን።

የመጀመሪያዎቹ 17 መጽሐፍት (ከዘፍጥረት - አስቴር) በእነዚህ ጊዜአት ውስጥ ሕዝቡ እንዴት እንደኖሩና እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር አብሮ እንዴት እንደሰራ ሃሳብ የሚሰጡ ታሪካዊ መጻሕፍት ናቸው።

ስለ፡

- የሰዎች ፍጥረት እና ውድቀት፡ ዘፍጥረት 1-4
- ኖህ፡ ዘፍጥረት 6-9
- አብርሃም፡ ዘፍጥረት 12፡25
- ይስሀቅና እስማኤል፡ ዘፍጥረት 21-27
- ያዕቆብ፡ ዘፍጥረት 25-36
- ዮሴፍ፡ ዘፍጥረት 37-50
- ሙሴ ፡ ዘጸአት 1-
- ዳዊት 1 ሳሙኤል 16-

አንብብ (ብዙዎቹ መዝሙሮችም በዳዊት ተጽፈዋል።)

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስድስት የግጥም መጽሐፍትንም እናገኛለን (ኢዮብ፣ መዝሙራት፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልዬ መኃልይና ሰቆቃው ኤርምያስ)። በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ደራሲዎቹ

ስለ ትግሎቻቸውና ስለ ስሜቶቻቸው በጣም ግልጽ ናቸው። ከእግዚአብሄር የቱንም ነገር መደበቅ እንደሌለብን ያሳዩናል።

ሦስተኛው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቡድን ነብያት ናቸው። እነዚህ ሰዎች በመከራ ጊዜአት መልእክት ከእግዚአብሔር ተቀብለው ያመጣሉ። ሕዝቡ መስማት ስለማይፈልጉ ከእነርሱ አንዳንዶቹ ተሰደዋል። አራት ታላላቅ ነብያት (ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ህዝቅኤል እና ዳንኤል) እና 12 ታናናሽ ነብያት አሉ።

የአዲስ ኪዳን አጭር መግለጫ

አዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ህይወትና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ስላለው ጊዜ የሚያስተምሩንን 27 ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ይይዛል።

የመጀመሪያዎቹ 4 መጻሕፍት ወንጌላት ናቸው የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስ ኤንጅል እና የዮሐንስ ኤንጅል ደግሞ ውልደቱን፣ አገልግሎቱን፣ አስተምህሮቱን፣ ተዐምራቱን፣ የደቀ መዛርቱን አጠራር፣ መከራውን፣ መስቀሉንና ትንሳኤውን በማካተት የመሲሁን የኢየሱስን ታሪክ ይነግረናል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መካከለኛ ነው። በኢየሱስ ህይወት አማካኝነትም እግዚአብሔርን እናውቀዋለን።

- የኢየሱስ ውልደት፡ ሉቃስ 2
- ኢየሱስ እና ደቀ መዛሙርቱ፡ ሉቃስ 5
- ከኢየሱስ ትምህርቶች ጥቂቶቹ፡ ሉቃስ 8፡40-56
- የኢየሱስ ሞት፡ ሉቃስ 22፡47-22
- የኢየሱስ ትንሳኤ፡ ሉቃስ 24

የሐዋርያት ሥራ በቀጥታ ከወንጌላት ቀጥሎ ይገኛል። ይህም ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ስለ ኢየሱስ ተከታዮች የሚናገር መጽሐፍ ነው። ሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተከታታይ ታሪክ ነው። በስደት፣ በመከራና በስኬት መካከል ሐዋርያቱ ለ50 አመት ገደማ የኢየሱስን ሥራ እንዲቀጥሉ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደረዳቸው ማንበብ እንችላለን።

ሐዋርያት ሥራን የሚከተሉት 22ቱ መጻሕፍት በተለያዩ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ለሚገኙ አማኞች የተጻፉ ደብዳቤዎች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ 13 ደብዳቤዎች “የጳውሎስ መልእክቶች” ተብለው ይጠራሉ ደግሞም የክርስትና የመጀመሪያው የሥነ መለኮት አስተማሪና የተሳካለት የወንጌል መልእክተኛ ስለሆነው ስለ ጳውሎስ የተጻፉ ደብዳቤዎች ናቸው።

ከጳውሎስ መልእክት በመቀጠል የሚገኙት ሰባቱ ደብዳቤዎች ከተወሰኑ ከቤተ ክርስቲያን ማህበረሰቦች ይልቅ በአጠቃላይ ለአብያተ ክርስቲያናት የተጻፉ ናቸው። የእነዚህ ደብዳቤዎች ደራሲያን የኢየሱስ ወንድምና በኢየሩሳሌም ያለው የክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነው ያዕቆብ፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ እና በሌላ ስፍራ ከኢየሱስ ወንድሞች አንዱ እንደሆነ የተገለጸው የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ ናቸው።

የአዲስ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ፣ የአዲስ ኪዳን ብቸኛው ራዕያዊ ጽሑፍ የሆነው የራእይ መጽሐፍ ነው። ከሮማ ግዛት ስር በስደት በነበረው በሐዋርው ዮሐንስ የታየውን ኃይለኛ ራእይ ይገልጻል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም የታወቁ ክፍሎች፡

አስርቱ ትእዛዛት፡ ዘጸአት 20፡1-7
የእግዚአብሔር ቡራኬዎች፡ ዘሁልቅ 6፡24-26
እግዚአብሄር እረኛዬ ነው፡ መዝሙር 23
የኃጢአት ኑዛዜ፡ መዝሙር 51
የኢየሱስ የመከራ ትንቢት፡ ኢሳይያስ 53
የተራራው ስብከት፡ ማቴዎስ 5-7
ብጹአኑ፡ ማቴዎስ 5፡1-12
የጌታ ጸሎት፡ ማቴዎስ 6፡9-13
ወርቃማው ህግ፡ ማቴዎስ 7፡12
ታላቂቱ ትዕዛዝ፡ ማቴዎስ 22፡35-40
ታላቁ ተልእኮ፡ ማቴዎስ 28፡18-20
የኢየሱስ ውልደት፡ ሉቃስ 2፡1-20
ደጉ ሳምራዊ፡ ሉቃስ 10፡25-37
መንፈሳዊ ስጦታዎች፡ 1 ቆሮንቶስ 12-14
የፍቅር መንገድ፡ 1 ቆሮንቶስ 13
ትንሳኤ፡ 1 ቆሮንቶስ 15
የመንፈስ ፍሬዎች፡ ገላትያ 5፡22-23
የእግዚአብሔር ጦር፡ ኤፌሶን 6፡10-18
የእምነት አርበኞች፡ ዕብራውያን 11
አዲስ ሰማይና ምድር፡ ራዕይ 21፤1-8

የኢየሱስ ምሳሌዎች

ኢየሱስ ሲያስተምር ብዙ ጊዜ በምሳሌዎች ይናገር ነበር አሁንም እኛ እነዚህን ታሪኮች ማንበብ እና ከእነርሱ ውስጥ አስፈላጊ መልእክቶችን መረዳት እንችላለን።

ማቴዎስ፡

ጨውና ብርሃን፡ 5፡13-16
በአለት ላይ የተመሠረተው ቤት፡ 7፡ 24-27
ዘሪው፡ 13፡1-9፣ 18-23
አረሞቹ፡ 13፡24-30፣ 36-43
የሰናፍጭ ቅንጣት፡ 13፤31-32
እርሾው፡ 13፡33-35
ሀብትና እንቁው፡ 13፡44-46
መረቡ፡ 13፡47-50
ቂመኛው አገልጋይ፡ 18፤23-35
የወይኑ ሥፍራ፡ 20፡1-6
ሁለቱ ልጆች፡ 21፡28-32
ጨሰኞቹ፡ 21፡33-46
የሰርጉ ግብዣ፡ 22፡1-14
10ቱ ቆነጃጅት፡ 25፡1-13
መላእክቶቹ፡ 25፡14-30
የመጨረሻው ፍርድ፡ 25፡31-46

ሉቃስ

ደጉ ሳምራዊ፡ 10፡25-37
ሞኙ ባለጸጋ፡ 12፡16-21
ታላቁ ግብዣ፡ 14፡15-24

የጠፋው በግ፡ 15፡1-7
የጠፋው ሳንቲም፡ 15፡ 8-10
የጠፋው ልጅ፡ 15፡11-32
ያልታመነው አስተዳዳሪ፡ 16፡1-13
ባለጸጋው ሰውና አላዛር፡ 16፡19-31
ነዝናዛዋ መበለት፡ 18፡1-8
ፈሪሳዊውና ቀራጭ ሰብሳቢው፡ 18፡9-14

ዮሐንስ

መልካሙ እረኛ፡ 10፤1-16
እውነተኛው ወይን፡ 15፡1-6
የእግዚአብሔር ባህሪያት
እነዚህ ከእግዚአብሄር ባህሪያት ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና የእግዚአብሄርን መገለጫዎች ስትጸልይ፣ እርሱን ለማመስገን እና ለማከበር መጠቀም ትችላለህ። “ፈጣሪዬ ስለሆንክ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ። ስለታማኝነትህና ስለፍቅርህም አመሰግንሃለሁ።አንተ አባቴ ነህ . . .”

እግዚአብሔር፡

አንዱ አምላክ: 1ጢሞ 2:5፣ ዮሐንስ 17:3፣ ሮሜ 3:30
ብቸኛው አምላክ: Jes 42:10-13፣ 44:6-8፣ 1 Kor 8:4-6፣ ይሁዳ 25
ፈጣሪ: 1 Mos.1፣ መዝሙር 33፣ ቆላስየስ 1:15-17
ታማኝ: 5 Mos 7:9፣ 32:4፣ 2 ተሰሎንቄ 3:3፣ 2 ጢሞቴዎስ 2:11-13
ፍቅር: መዝሙር 103፣ ሮሜ 5:8 ጀምሮ 1 ዮሐንስ 4:7-21
አባታችን: Jes 63:16፣ ማቴዎስ 6:8፣ ማቴዎስ 7:11፣ ሮሜ 8:15-17
ቅዱስ: መዝሙር 99፣ Jes 6:1-5፣ 1 ጴጥሮስ 1:15 ጀምሮ፣ ራእይ 15:3 ጀምሮ
ዘላለማዊ: ኀሀምያ 9:5፣ መዝሙር 90 1-4፣ 93:2፣ 1 ጢሞቴዎስ 1:17፣ 2 ጴጥሮስ 3:8
ጻድቁ: መዝሙር 11:7፣ 33:4 ጀምሮ፣ ዮሐንስ 17:25፣ 2 ጢሞቴዎስ 4:8፣ ራዕይ 15:3 ጀምሮ
ሁሉን ቻይ: 1 ዜና 29:10-13፣ ኤርምያስ 32:17፣ ማቴዎስ 28:18፣ ራዕይ 1:8
የማይደፈር: መዝሙር 139:1-18፣ Jes 55:8-11፣ ሮሜ 11:33-36
በኢየሱስ የተገለጠ: ዮሐንስ 14:8-11፣ ቆላስየስ 1:15-20፣ ዕብራውያን 1:1-3፣ Jes 9:2-6
ጥንቃቄ የተሞላ: መዝሙር 23, 40:18፣ ማቴዎስ 6:25-34፣ 10:28-31፣ 1 ጴጥሮስ 5:7
ፈራጁ: Jes 33:22፣ ማቴዎስ 25:31-46፣ ሐዋርያት ሥራ 17:31፣ ያዕቆብ 4:12
የኃጢአተኞች ወዳጅ: ሉቃስ 15:10፣ 15:21-24፣ 19:10፣ ማቴዎስ 9:9-13፣ 1 ጢሞቴዎስ 1:15
ስላሴ: ማቴዎስ 3:16 ጀምሮ፣ 28:19፣ ዮሐንስ 10:30፣ ሮሜ 8:9፣ 1 ቆሮንቶስ 12:4-
6, 2 ቆሮንቶስ 13:13, 1 ጴጥሮስ 1:2, ዘፍጥረት 1:26
የማይለወጥ: ዕብራውያን 1:10-12
መጽናናት: 2 ቆሮንቶስ 1:3-5
ጸጋን የተሞላ: ኤፌሶን 2:4-10
የማይታይና የማይሞት: 1 ጢሞቴዎስ 6:15 ጀምሮ

ለደካሞች ቅርብ የሆነ: Jes 57:15
ታሪካችን: ዳንኤል 2:20-22
ተአምራትን የሚሰራ: መዝሙር 86:10
የሚሰጥ: 1 ዮሐንስ 1:9
ሰላም: 2 ተሰሎንቄ 3:16
ክፋትን የሚጠላ: Jes 61:8
የሚባላ እሳት: ዕብራውያን 12:28 ጀምሮ
ስሞታችንን የሚቀበል: መዝሙር 13
ነው።

ኢየሱስ ማን ነው?

በክርስቶስ አማካኝነት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ማወቅ እንደምንችል ተጽፎአል። ስለዚህ እነዚህ የኢየሱስ ደግሞም የእግዚአብሔር የራሱ መገለጫዎች ናቸው።

መልካሙ እረኛ: ዮሐንስ 10:11
የእግዚአብሔር በግ: ዮሐንስ 1:29
መንገዱ፣ እውነቱ እና ህይወቱ: ዮሐንስ 14:6
ድንቅ መካር፣ ታላቅ አምላክ፣ የዘላለም አባት፣የሰላም ንጉስ: ኢሳይያስ 9:6
ቃል: ዮሐንስ 1:1
አለቱ: 1 ቆሮንቶስ 10:4
የክብር ጌታ: 1 ቆሮንቶስ 2:8
ቅዱስና ጻድቅ: ሐዋርያት ሥራ 3:14
ነጻ አውጪ: ሮሜ 11:26
ህይወታችን: ቆላስያስ 3:4
የሚቤዠኝ: ኢዮብ 19:25
የህይወት ራስ: ሐዋርያት ሥራ 3:15
አልፋና አሜጋ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው: ራዕይ 22:13
ሕይወት: ዮሐንስ 14:6
የአለም ብርሃን: ዮሐንስ 8:12
የሕይወት እንጀራ: ዮሐንስ 6:35
ይይሁዳ አንበሳ: ራእይ 5:5
ሕያው: ራእይ 1:18
በእግዚአብሔርና በሰው መሀል ያለ መካከለኛ: 1 ጢሞቴዎስ 2:5
እውነተኛው አምላክ: 1 ዮሐንስ 5:20
የእስራኤል ንጉስ: ዮሐንስ 1:49

ጌታና አዳኝ: 2 ጴጥሮስ 2:20
የማዕዘን ድንጋይ: ኤፌሶን 2:20
ህያው ቃል: 1 ዮሐንስ 1:1
የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ: ዕብራውያን 12:2

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ኢየሱስ የተነገረ ትንቢቶች

ኢየሱስ ከመወለዱ ከብዙ ሺ አመታት በፊት እንደሚመጣ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጠ።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለሚመጣው መሲህ ከተነገሩት መካከል እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው፡

የብሉይ ኪዳን ትንቢት	የሰዲስ ኪዳን ፍጻሜ
በቤተልሄም ተወለደ	ሚክያስ 5:2	ማቴዎስ 2:1-6, ሉቃስ 2:4
ኃያልና ዘላለማዊ	ኢሳይያስ 9:6-7	ሉቃስ1:31-33
ከድንግል የተወለደ	ኢሳይያስ 7:14	ማቴዎስ 1:18-23
ከይሁዳ ነገድ	ዘፍጥረት 49:10	ራእይ 5:5
የልጆች መገደል	ኤርምያስ 31:15	ማቴዎስ 2:16-18
ወደ ግብጽ መሸሽ	ሆሴዕ 11:1	ማቴዎስ 2:15
መቅደስን ማጽዳት	መዝሙር 69:10	ዮሐንስ 2:13-17
ወደ ኢየሩሳሌም መግባት	Sak. 9:	ማቴዎስ 21:1-11
ሰላሳ ብር	Sak. 11:12-13	ማቴዎስ 26:15, 27:3-10
በመከራ ጊዜ ዝምታ	ኢሳይያስ 53:7	ማቴዎስ 26:62, 27:12-14
ለጠላቶች መጸለይ	ኢሳይያስ 53:12	ሉቃስ 23:34
ለልብሱ ዕጣ	መዝሙር 22:19	ማቴዎስ 27:35
በባለጸጋው ሰው መቃብር መቀበር	ኢሳይያስ 53:9	ማቴዎስ 27:57-60
በእኛ ፋንታ መሰቃየትና መሞት	ኢሳይያስ 53:4-12	ማቴዎስ 8:17, ሮሜ 4:24, 1 ቆሮንቶስ 15:3, 2 ቆሮንቶስ 5:21, 1 ጴጥሮስ 2:22-24, 3:18

በመስቀል ላይ ምን ተከናወነ?

ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን። ወደ ገነት ማንም መግባት አይችልም፣ ወይም በዚህ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ቅረብ። ኃጢአተኞች ነን ደግሞም በዚህ ምክንያት መቀጣት ነበረብን።

ኢየሱስ፣ ብቸኛው ጻድቅ ሰው፣ በአንተ ፋንታ ተቀጥቷል ደግሞም ሞቷል። ቅጣትህን ወስዷል ደግሞም በኃጢአትህ ምክንያት ሞቷል። ነገር ግን እርሱ ሞትንና ክፉን አሸንፏል ደግሞም ከሞት ተነስቷል! የኢየሱስ ድል የእኛ ድል ስለሆነ፣ከዚህ በኋላ ሞት ወይም ክፉ ማንንም መያዝ አይችልም። ከዚህ በኋላ ከኃጢአት በታች የምንኖር ባሮች አይደለንም። ኃጢአታችንን እንዲወስድ ኢየሱስን ከጠየቅነው በእርሱ ደም አማካኝነት ነጻ ሆነናል!

- ብዙ ሰዎች ለአምላካቸው መስዋእት አድርገው እንስሳትን ያርዳሉ። ከእንስሳቱ ሞት የተነሳ እግዚአብሄር ኃቲአታቸውን ይቅር እንዲላቸው ተስፋ ያደርጋሉ። ኢየሱስ ኃጢአታችንን የሚያስተሰርይ ፍጹም በግ እንደሆነ ተገልጾአል። ፩ ቆሮንቶስ 5፡7፣ ኤፌሶን 5፡2፣ ሮሜ 3፡24-25፣ ዕብራውያን 9፡27-28፣ ራዕይ 2፡12- ጀምሮ
- ከእግዚአብሄር ጋር ያለን ግንኙነት ታድሷል ደግሞም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ጠላትነት በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ተወግዷል። ሮሜ 5፡10፣2 ቆሮንቶስ 5፡ 18-20፣ ቆላስየስ ፩፡21-22።
- ኢየሱስ ሰይጣንን በመስቀል ላይ አሸንፎታል ደግሞም ከኃጢአትና ከክፉ ቀንበር ዋጅቶናል። ቆላስየስ 2፣15፣ ፩ ቆሮንቶስ 6፣20፣ ኤፌሶን ፩፡7፣ ፩ ጴጥሮስ ፩፡18 ጀምሮ፣ ራዕይ 5፡9፣ ማርቆስ 10፡45።

- ኢየሱስ በእኛ ፈንታ ቅጣታችንን (የዘላለም ሞትን) ስለወሰደ ጸድቀናል ሮሜ 3፡23-24፣ 5፡1፣ 5፡9፣ ገላትያ 2፤16፣ ፩ ቆሮንቶስ 6፡11፣ ኀሰ 53፤11፣ ኤፌ.ሶን 1፡7
- በመስቀል ላይ ከተሰራው ሥራ የተነሳ እግዚአብሔር ልጆቹ ሊያደርገን ይችላል። አሁን የእርሱ ልጆች ነን። ሮሜ 8፡15-17፣ ገላትያ 4፡4-7፣ ኤፌ.ሶን 1፡5
- እግዚአብሄርን ለመገናኘት ርቆ መጓዝ ያስፈልጋል ደግሞም በአንድ አቅጣጫ ብቻ መመላለስ የለብንም። በየትኛውም ስፍራና ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር እንድንገናኝ ኢየሱስ በሩን ስለከፈተልን፣ እግዚብሔር በመቅደስ አልተሸፈነም ደግሞም በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆም ምንም ነገር የለም!አሁን እርሱ በውስጣችን አለ። ማቴዎስ 27፡51፣ ዕብራውያን 4፤16፣ ፩ ቆሮንቶስ 3፤16፣ ማቴዎስ 28፡20።

በኢየሱስ በማመኔ እኔ . . . ነኝ

የኋላ ታሪክህ ወይም ሁኔታዎችህ ምንም ይሁኑ፣ እነዚህ የሚከተሉት ጥቅሶች እውነተኛ ናቸው። በኢየሱስ ከታመንክ ደግሞም ለእርሱ ከተማረክህ ይቅር ተብለሃል። ጻድቅ ነህ ደግሞም ከኩነኔ ነጻ ነህ! በኢየሱስ በማመን፣ አንተ . . .

- ይቅር የተባልክ ነህ: ሐዋርያት ሥራ 10:43
- ጻድቅ ነህ: ሮሜ 3:26
- በጸጋ የዳንክ ነህ: ኤፌሶን 2:8-9
- አዲስ ፍጥረት ነህ: 2 ቆሮንቶስ 5:17
- ብርሃንና ጨው ነህ:ማቴዎስ 5:13-
- የእግዚአብሔር መቅደስ ነህ:ነ ቆሮንቶስ 3:16
- ለእርሱ የምትኖር ነህ፣ ሮሜ 14:8
- ከኩነኔ ነጻ ነህ፣ሮሜ 8:1-
- የእግዚአብሔር የተወደድክ ልጅ ነህ፣ ኤፌሶን 5:1
- የገነት ዜጋ ነህ፣ ፊሊጲስዩስ 3:20

- ከሞት ወደ ህይወት የተሻገርክ ነህ ፣ዮሐንስ 5:24
- ነጻ ነህ: ዮሐንስ 8:31, 32, 36
- ሁልጊዜ የተጠበቅህ ነህ፣ ሮሜ 8:35-39
- ህያው ነህ ፣ 1 ዮሐንስ 5:12-
- ከእግዚአብሔር ጋር የተስማማህ ነህ፣ ሮሜ 5:1

በተለያዩ ሁኔታዎች የሚነበቡ ጥቅሶች ...

- ደስተኛ ስሆን

መዝሙር 33-34፣ *መዝሙር* 145፣ *መዝሙር*148

- ስፈራ

ዮሐንስ 14:1፣ ዮሐንስ 14:27፣ *መዝሙር* 56:4-፣ *መዝሙር*118:5-9፣ ኢሳይያስ 41:10,13

- ሞትን ስፈራ

ሮሜ 8:35-39፣ ሮሜ 14:8፣ ዮሐንስ 11:25-፣ ዮሀንስ 14:1-፣ *መዝሙር* 23:4

- ብቸኛ ስሆን

መዝሙር 25:14፣ *መዝሙር* 27:7-10፣ *መዝሙር* 139፣ *መዝሙር* 142፣ *መዝሙር* 41:10፣ ኢሳይያስ 49:14-16፣ ዘዳግም 31:8፣ 2 ቆሮንቶስ 4:7-5:10

- ስሰደድ

ማቴዎስ 5:10-12፣ ሐዋርያት ሥራ 5:41፣ *መዝሙር* 140፣ ኢሳይያስ 51:7 ጀምሮ፣ 2 ጢሞቴዎስ 3:12፣ 1
ጴጥሮስ 4:12፣ ሮሜ 8:35፣ 2 ቆሮንቶስ 4:16-18

- በስደኋ ላይ ስሆን

መዝሙር 91፣ *መዝሙር* 118:5-9፣ *መዝሙር* 18:2-4፣ *መዝሙር* 121:5-8፣ ሮሜ 8:35-39

- ስርዳታ ስፈልግ

መዝሙር 32፣ *መዝሙር* 51፣ *መዝሙር* 121፣ *መዝሙር* 142፣ *መዝሙር* 13፣ *መዝሙር* 86:4-7፣ *መዝሙር* 130፣ 1 ዮሐንስ 1:9፣ ኢሳይያስ 1:18፣ ማቴዎስ 11:28-30

- ስደክም

ኢሳይያስ 40:28-31፣ 1 ቆሮንቶስ 1:26-31፣ 2 ቆሮንቶስ 12:9-፣ *መዝሙር* 138:3-8

- ስታመምና ስደክም

መዝሙር 6፣ *መዝሙር* 13፣ *መዝሙር* 42፣ *መዝሙር* 86፣ 2 *መዝሙር*

12:9-

- ስለ ደህንነቴ እርገጠኛ ሳልሆን ስቀር

ዮሐንስ 5:24፣ ዮሐንስ 6:47፣ 1 ዮሐንስ 5:11-13፣ ሮሜ 10:9-10

- ስጠፈጠር

ዮሐንስ 20:24-29፣ ማቴዎስ 11:2-6፣ ማርቆስ 9:23-፣ 2 ቆሮንቶስ 4:18፣ 2 ቆሮንቶስ 5:7፣ ኢሳይያስ 45:9-12

- ስሳምን ስፈልግ

ዘሑልቅ 6:25- ፣ ኤርምያስ 29:11-13፣ መዝሙር 85:9፣ ፊሊጲስዩስ. 4:6-፣ ሰቆቃው 3:21-

26፣ ዮሐንስ 14:27፣ ዮሐንስ 16:33

- ጥብብ ሲያስፈልገኝ

ያዕቆብ 1:5-፣ ምሳሌ 2:1-8፣ ምሳሌ 9:10፣ ኤፌሶን 1:17-19

- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ስፈልግ

ሚኪያስ 6:8፣ መዝሙር 25:4-14፣ ምሳሌ 3:2-7፣ ኤርምያስ 29:11-13

- የእግዚአብሔርን ስጦታ ማወቅ ስፈልግ

1 ቆሮንቶስ 2:12 (መንፈስ ቅዱስ)፣ ኢሳይያስ 41:10 (ብርታት)፣ ዮሐንስ 14:27

(ሰላም)፣ 1 ቆሮንቶስ 10-13 (ከአቅም በላይ የሆነ ፈተና የለም)

የምንናርቧቸው የተስፋ ቃሎች

ዘዳግም 31:8 * 2 ዜና 7:14 * መዝሙር 9:10- * 16:11 * 34:19 * 55:23
* 103:11- * 121 * 145:18 * ኢሳይያስ 41:10, 45:3, 49:15 * 57:15 *
ኤርምያስ 17:7- * 24:7 * 29:11-13 * ሰቆቃው 3:21-26 * ሕዝቅኤል 34:15- *
36:26- * ሶፎንያስ 3:17 *ማቴዎስ 7:7- * 10:28-31 * 11:28- * 18:19-
20 * ማርቆስ 10:29- * ሉቃስ 1:37 * ዮሐንስ 5:24 * 6:35, 40 * 8:12፣
31- * 10:27-28 * 11:25-26 * 14:27 * ሮሜ 8:15-17 * 8:28, 35-39 * 14:8 * 1ቆሮንቶስ 10:13 * 2 ቆሮንቶስ 9:8 * ዕብራውያን 7:25 * 13:5 *
ራዕይ 21:1-7

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ጸሎቶች

ማቴዎስ 6:5-15፣ ዘዳግም 9:25-29፣ 2 ሳሙኤል 7:18.29፣ 1 ዜና 29:10-19፣ ዕዝራ 9:5-15፣ ነህምያ 1:5-11፣ ኢሳይያስ 64:1-11፣ ኤርምያስ 20:7-13፣ ዳንኤል 9:4-19፣ ዮናስ 2፤2-10፣ ሐዋርያት ሥራ 4:24-30፣ 1 ተሰሎንቄ 3:10-13፣ ኤፌሶን 1:15-23፣ ኤፌሶን 3:14-21፣ ዮሐንስ 17፣ መዝሙር 51 እና ሌሎቹ ሁሉም መዝሙሮች።

ለምንድን ነው ወንጌሉን ከሌሎች ጋር መካፈል ያስፈን?

እግዚአብሄር ሰውን ሁሉ ስሚወድና ሊያድናቸው ስለሚፈልግ ፡ ዮሐንስ 3:16።
እግዚአብሔር ወንጌሉን እንድንናገር ያዘናል፡ ማቴዎስ 28:18-20፣ ሐዋርያት ሥራ 1:8

ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ ብቸኛው መንገድ ነው፣ ምንም አይነት ሌላ ሃይማኖት ማዳን አይችልም፡ ዮሐንስ 14:5፣ ሐዋርያት ሥራ 4:12
የሰው ዘር ውድቀት ሐቅ ነው፣ እያንዳንዱ ሰው ደህንነት ያስፈልገዋል፡ ማቴዎስ 7:13፣ 2 ተሰሎንቄ 1:8-9
የሰው ዘር ሁሉ ከእግዚአብሄር ጋር መታረቅ አለበት፡ 2 ቆሮንቶስ 5:19-20፣ ቆላስየስ 1:21-22

እግዚአብሄር ሰውን ሁሉ፣ ህዝብን ሁሉ ደግም ቋንቋን ሁሉ ይወዳል፡

ዮሐንስ 3:16፣ ማቴዎስ 24:14፣ ማቴዎስ 28:18-፣ ማርቆስ 16:15፣ ሉቃስ 24:46-፣ ሮሜ 10:12-15፣ ሐዋርያት ሥራ 1:8፣ 7:9-10፣ 13:47፣ 26:16-18፣ መዝሙር 96፣ ሮሜ 15: 8-13፣ 1 ዜና 16: 23-31፣ ራዕይ 7:9

ጠንጋላቱ

እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና ጥያቄዎች ገና ወንጌልን ከማያውቅ ሰው ጋር ሆኖ ለማንበብ ጥሩ ናቸው፡

- ሮሜ 3:23 ኃጢአተኛ ማነው?
- ኢሳይያስ 59:2 በህጸጠትህ ውስጥ ኃጢአት ምን አደረገ?
- ዕብራውያን 9:27 ስትሞት እንዲሆን የምትፈልገው ምንድን ነው?
- ኤፌሶን 2:8-9 እንድትድን ያስፈለህ ነገር ምንድን ነው?
- ሮሜ 5:8፣ ሮሜ 6:23 ኢየሱስ ለእኛ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?
- ዮሐንስ 1:12 የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ምን ማድረግ እንችላለን?
- ራዕይ 3:20 አሁን ኢየሱስ የት ነው ያለው? ምን እያደረገ ነው? እንተ ምን ማድረግ አለብህ? ታደርገዋልህን?
- ዮሐንስ 5:24 በሰማህ እና ባመንህ ጊዜ ምን ተከናወነ?